# “ውሸትና ስንቅ እያደረ ይቀላል”!!!

ከባህልቢ ዘማርያም

ክፍል ሰባት፤

(በሐጎስ ዮሐንስ ፅሑፍ ውስጥ በ8ኛ ፓራግራፍ ከአንደኛ መስመር ጀምሮ እንደሚከተለው የሚል ሰፍሮ ይገኛል፡)

> *“ለመጥፎም ለደጉም ስሜትንና አስተያየትን መለዋወጡ መልካም ነገር ነው። በመሆኑም ካገር ቤት እንደተመለስኩ **ይህንን ግኙቴን** ለተወሰኑ በአሜሪካን አገር ነዋሪ ባለመዋሉቼና ታማኝ ጓደኞቼ አጋራሁዋቸው። ያኔ ይህንን **አሉባልታና** (rumors)_**ያልተጣራ ውንጀላ** (allegations) ለመስማት የመጨረሻ ሰው መሆኔ እጅጉን አሳፈረኝ።”*

ድሮስ! “ጉድ ሳይሰማ መስከርም አይጠባም” ይባል የለ! ሐጎስ ዮሐንስ አሉባልታና ያልተጣራ ውንጀላን ያነገበ የሐሜት ወሬን “ለመስማት የመጨረሻ ሰው” በመሆናቸው ማፈራቸውን በቁጭት ይገልጻሉ። እውነቱን ለመናገር አንባቢ ምን እንደሚል ለመስማት የሚያጓጓ ቢሆንም፣ በዚህ ፀሐፊ እይታ ይህ ዓይነት ቁጭት ከጤነኛ ሰው የሚጠበቅ አይደለም። በመጀመርያ ደረጃ ጥሩም ሆነ መጥፎ ወሬ ለመስማት የመጨረሻ ሰው መሆን ለምን ሊያሳፍር እንደሚችል ግልጽ አይደለም። በሁለተኛ ደረጃ ወሬውን ለመስማት የመጨረሻ ሰው መሆን እውነት የሚያሳፍር ሆኖም ከተገኘ፤ ከሳቸው በኋላ በሳቸው አማካኝነት የሰማን ወገኖች አለንና እኛ እንፈርላቸው እንጂ፤ ሐጎስ ዮሐንስ ምን ገዶዋቸው ነው የሚያፍሩት? እርሳቸው ሐሜትና አሉባልታን ለመስማት ከጓደኞቻቸው የመጨረሻ ሰው ሆንኩ ብለው ቢበግኑም፤ እኛ ደግሞ እሳቸው “ሰምተው” ጽፈው ለንባብ ካበቁት በኋላ ነው አንብበን ያወቅነው። ስለሆነም የቆየ የተጠናወታቸው ውሸትን የማናፈስ ልምድ ኖሯቸው ካልሆነ በስተቀር ሐሜትና አሉባልታውን ለመስማት የመጨረሻ ሆንኩኝ ብሎ ማዘን ጭራሽ አላስፈላጊ ነው። ይህ ፀሐፊ የሐጎስ ዮሐንስን ፅሑፍ ካነበበ በኋላ እውነት አንድን ነገር ዘግይቶ መስማት ያሳፍራል እንዴ! ብሎ ትንሽ ማሰላሰሉ አልቀረም። አንባቢዎች! ምን ዓይነት ጅል ነው አንድን ፍጻሜ ለመስማት የመጨረሻ መሆን ያሳፍራል ኢያሳፍርም ብሎ ለማሰላሰል ጊዜውን የሚያጠፋ ብላቹህ ትፈርዱ ይሆናል። አያድርስ ሲባል ሰምታችሁ ይሆናልና፤ አያድርስ ስለደረሰ ነውና ባትፈርዱ መልካም ነው። እንፈርዳለን ካላቹህም የራሳቹህ ጉዳይ ነው! የፈለጋቹህን ብትሉም፤ ፀሐፊው ግን መልሱን አግኝቶታል። የኸውም፤ ይህ አሉባልታና ያልተጣራ ውንጀላ አሁን በወረቀት ሰፍሯል ወደ ሕብረተ-ሰቡም ተሰራጭቷል። ስለሆነም፤ “ወረቀትና ሞኝ የያዙትን አይለቁም” ይባላልና ይህ ወረቀት ለሚመጣው ትውልድም ይተላለፋል። እንዲህ ከሆነ ደግሞ የሐጎስ ዮሐንስን እይታና ሚዛን ለመገመት ባይችልም፤ ይህ ጸሐፊ ከሱ በኋላ የሚመጡ ትውልዶች ሁሉ እየተቀባበሉ ስለሚያነቡትና ስለሚሰሙት እንዲሁ ተስቆበት የሚታለፍ ሳይሆን በህብረተ-ሰብ ውስጥ ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ ባጭሩም ቢሆን የማሳትን አስፈላግነት በሚገባ ተገንዝቦታል።

ስለሆነም፤ አሉባልታና ሐሜት ላይ ተመሥርቶ የሚነዛ ቅጥፈት ለአንድ ሕብረተ-ሰብ ሰላማዊ ኑሮና እርስበርስ መተማመን ላይ ሊያስከትለው የሚችለውን ጫና ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፤ የሐጎስ ፅሑፍ ሳይተች መታለፍ የለበትም። ሌባ የሚጎዳው የተሰረቀውን ሰው ብቻ ሲሆን ውሸትና አሉባልታ ግን አገርና ህዝብን ያባላል። ይህ ማለት ሌብነት ደግ ነው ማለት ሳይሆን በአንጻራዊነት ሲታይ የሚያደረሰው ጥፋት ተወስኖ ይቀራል ለማለት ነው። ውሸት ግን እንደሰደድ እሳት ከዳር እስከዳር ያዳርሳል፤ በዚህም ይዋል ይደር እንጂ ነጥሮ መውጣቱ የማይቀረው እውነት ቦታውን

እስኪተካ ድረስ በሕብረተ-ሰብ ውስጥ ሊፈጥረው የሚችል ቀውስ፣ የርስበርስ ጥርጣሬና ጥላቻ በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ሐጎስ ዮሐንስ በፅሑፋቸው ውስጥ ለመስማት የመጨረሻ በመሆናቸው አፈርኩበት ያሉት  አሉባልታና ሀሜት ግን “አውቆ የተኛ ቢቀሰቅሱት አይነሳም” እንደሚባለው እውነቱን ሳይሆን ለማመን የሚፈልጉትን ለሚያምን ካልሆነ በስተቀር እውነቱን ለሚፈልግ ሰው የተጻፈውን ዝባዝንኬ እንዳነበበ ግልጽ እንደሆነለት አያጠራጥርም። ድሮስ ራሳቸው ፀሐፊው “አሉባልታና ሐሜት” (rumors and Allegations) ያሉትን የሚያምን ጤነኛ ሰው እንዴት ይኖራል!? ለማነኛውም፤ ሐጎስ ዮሐንስ በራሳቸው ብእር ያሰፈሩት አሉባልታና ተባለ! ተባለ! ተራ የአሳባቂዎች መለያ ባሕሪ ውስጥ ራሳቸው የአንበሳ ድርሻ እንዳላቸው ከራሳቸው ብእር የበለጠ ምስክር ሊገኝ እንደማይችል እዚህ ቁልጭ ብሎ ሰፍሯልና ሊያሳፍራቸው የሚገባው ጉዳይ ይህ ነበር። ይህ ባሕሪ በቁስ አካላቸው ውስጥ ባይኖር ኖሮ፤ አሉባልታን ሰማሁ ብለው በዛ መነዳት ሳይሆን የሚጠበቅባቸው፤ ያንን ማስተካከልና አሉባልታና ሐሜትን ሥራ ብለው የያዙ <u>“ታማኝ ጓደኞቼ”</u> የሚሉዋቸውን በመገሰጽ ማስተካከል በተገባቸው ነበር። ሳይሆን ቀረና፤ ራሳቸው የአሉባልታው ሰለባ ሆነው አረፉት። ከዛም አልፎ፤ ያልሆነውን፤ ጭብጥ ሊያቀርቡበት የማይችሉትን፤ የራሳቸው ኅሊና እንኳ ሊቀበለው ያልቻለውን ተራ አሉባልታ በመጻፍ የተወሰኑት የዋሆች ለማታለል በቅቷል። ይህ የማታለል ሙከራቸው በስሕተት የተፈጸመ ሳይሆን፣ ሆን ተብሎ የንጹሃን ሰዎች ስም ለማጉደፍና በማህበረ-ሰባችን ውስጥ አለመተማመንን ለማስረጽ በታማኝ ጓደኞቻቸውና አለቆቻቸው የተበጀጀ ሴራ ነው። ግን ምን ይደረግ አልቻሉበትም። መጨረሻ ላይ እውነትን መደበቅ አይቻልምና የጻፍኩት “አሉባልታና ሐሜት ላይ ተመርኵዞ ነው” በማለት ሃቁን አውጥተውታል። በዚህም ተግባራቸው የሳቸው ብጤዎች ካልሆኑ በስተቀር “ታማኝ” ያሉዋቸው ጓዶቻቸውም ሳይታዘቧቸው አልቀሩም። ከቀጠፉ አይቀር በዛው መጽናትም ያባት ነበር። ቀጥፎ ሲያበቃ “አሉባልታና ሐሜትን ለመስማት የመጨርሻ ሰው ሆንኩኝ” ብሎ መብከንከን፤ መናደድና መበሳጨት ግን የጤነኛ ሰው ምልክት አይደለም። የሆነ ሆኖ ሐጎስ ይህንን ጽሑፍ ያወጡት መስሎዋቸው ወይም በስሕተት ሳይሆን አውቀው ለክፋት ሲሉ የቀመሩት መሆኑን ከላይ በጥቅስ ውስጥ የተቀመጠው የብእራቸው ውጤት የሆነው አባባል ቁልጭ አድርጎ አሳይቶናል።

(ሐጎስ ዮሐንስ በዚህ አላበቁም። ቀጥለው በፅሑፋቸው ውስጥ በ8ኛው ፓራግራፍ ከ4ኛ መስመር ጀምሮ እንዲህ የሚል ሰፍሯል፡)

> *“ሆኖም ከነሱ ውስጥ አንዱም እንኳ ይህ አሉባልታ እውነት ሊሆን ይችላል ብሎ ያመነም እውነት ነው ብሎ የተቀበለም የለም። እኔም ብሆን እስካሁን ይህ ነገር እውነት ሊሆን ይችላል ብዬ ከልብ አላምንም።....... ”*

እዚህ ላይ ነበር “ብውነይ ዲየ እታ ብሕልመይ”! የሚለው የሐጎስ ገብረሕይወት ዘፈን ትዝ የሚለን! ሐጎስ ዮሐንስ አሉባልታና ያለተረጋገጠ ውንጀላ ሲወራ ለመስማት የመጨረሻ መሆኔ አሳፈረኝ ብለውን ሲያበቁ፤ አሁን ደግሞ በራሳቸው አንደበት እነዚህ ‘እንተማ ወደ ኋላ ቀርተሃል’ ያሉዋቸው “ታማኝ ጓደኞቼ” የሚሉዋቸው ወገኖች ራሳቸው ወሬውን እንዳላመኑትና እንዳልተቀበሉትም እዛው በዛው ያበስሩናል። ወቸ ጉድ! “ምን ተይዞ ጉዞ” ይባል የለ! ታዲያ ሐጎስ ዮሐንስ ምን ይዘው ነው ይህንን አሰልችና ድግግሞሽ የበዛበት 7 ገጽ የሚሆን መጣጥፍ ዓይጋና ኢሮብ ኦርግ ድረ-ገጾች ላይ የለጠፉት? “ታማኝ ባለመዋሎቻቸውም” ሆኑ እሳቸው ራሳቸው ያላመኑትና እውነት ነው ብለው ያልተቀበሉትን (የሰሙት ነገር ካለ ማለት ነው) እውነት አስመስለው ለመጻፍ ምን አነሳሳቸው? የሚለው ጥያቄ መመለስ የሚችሉት ሐጎስ ብቻ ናቸው። “ታማኝ ባለመዋሎቻቸውም” የሚያውቁት ነገር ካለ ጀባ ቢሉን ምርቃት ነው። የሆነ ሆኖ ይህንን ዓይነት እርስ በርሱ የሚጣረስ ጉድ ማንበብ

“አታ ብውነይ ዲየ! ብሕልመይ!” ያሰኛል። ምን ነው ወዳጄ! እርስዎም ራስዎ ይሆናል ብለው ካላመኑ፤ ታማኝ ጓደኞቹዎና ባለመዋሎቹዎም አላመኑም ለማረጋገጥም አልቻሉም ካሉን፤ ምን ይዘው ነው ታዲያ ይህንን ዝባዝንኬ ለመጻፍ የተነሳሱት? የት አለ ጭብጡ? ማፈርያ ከመሆን አድነን የሚባለው እንዲህ ዓይነት ጉድ ሲያጋጥም አይደለ!!!!

እንዲህ ዓይነት አስነዋሪ ተግባር ውስጥ በመሳተፍ የኢሮብ ወጣቶችን ለሻዓቢያ በመመልመል የኢሮብ ህዝብንም ሆነ ሌላ ኢትዮጵያዊ ወገኑን የሚያደማ አንድም እንኳ የኢሮብ ተወላጅ ይኖራል ብዬ አላምንም፤ አንድም የኢሮብ ተወላጅም ይህንን የሚያምን እንደሌለ አውቃለሁ፤ የሚለው የሐጎስ ዮሐንስ አባባል በጽሑፋቸው ውስጥ በተደጋጋሚ የሚታይ ቢሆንም፤ ተደጋገመ እንጂ ይዘቱ ተመሳሳይ በመሆኑ ደጋግሞ ማቅረቡ አንባቢን እንዳያሰለች ተያይዞ የቀረበውን የራሳቸውን ፅሑፍ እንዲያነብ ይጋበዛል።

ፓራግራፍ 9 ከ10ኛ መስመር ጀምሮ እንደሚከተለው የሚል ሰፍሮ ይገኛል፤

> *“ለኛ በባሕር ማዶ ለምንኖር የኢሮብ ተወላጆች ግልጽ መሆን የሚገባው ጉዳይ አሳዳጆችንን በመደገፍ የኢሮብ ህዝባችንና (በኢትዮጵያ) መንግሥታችን መካከል አለመግባባትን መፍጠር ፍትሐዊም ሕጋዊም አለመሆኑን ነው።”*

እዚህ ላይ አሳዳጆችንን መደገፍ የለብንም የሚለው ምክር ልብ ሊባልና ጆሮ ሊሰጠው የሚገባ ሓሳብ ነው። ከጽሑፉ ጠቅላላ ይዘት አንፃር ሲታይ “አሳዳጆችን” የሚለው ቃል ሻዓቢያ ላይ ያነጣጠረ ይመስላል። ስለሆነም፤ ሻዓቢያን በኢትዮጵያ ጠላትነት መፈረጁ ትክክል ይሆናል። በመሆኑም ከሻዓቢያ ጋር በመተባበር አገራችንንና ወገናችንን የሚጎዳ ሁሉ መወገዝ ይኖርበታል። ማውገዝ ሲባል ግለሰብን ወይም ድርጅትን ሳይሆን በመሠረቱ የሚወገዘው ወይም የሚወደሰው አስፈጽመዋለሁ ብሎ የቆመለት ዓላማና ተግባር ስለሆነ፤ ምክሩ ማትኰር የነበረበት የሻዓቢያን ዓላማና ስትራተጂ በሚደግፍ ግለሰብም ሆነ ድርጅት ላይ ነው። ዞሮ ዞሮ፤ ዋና ሚሥጢሩ ያለው እስትራተጂአዊ ዓላማው ላይ መሆኑ መዘንጋት የለበትም። ስለሆነም በጉዳዩ ላይ ወሳኝ ተራ ሊጫወቱ የሚችሉትን እነ አቶ መለስ ዜናዊና አቶ ስብሓት ነጋ ከነጭፍሮቻቸው ሃይ! ሊባሉ ይገባል። በነገራችን ላይ አቶ ስብሓት ነጋ ለድምፂ ወያነ የሰጡት ቃለ ምልልስ ህወሓት የሻዓቢያን ስተራተጂያዊ ግብ እስከምን ድረስ እንደሚደግፍ በግልጽ የሚያሳየን ስለሆነ፤ ይህንን ሊንክ ተጋብዟል።http://www.dimtsiwoyane.com/ewanawizaeba/Ewanawi23091999.asx እንዲያዳምጡ ከዚህ ቃለ-ምልልስ፤ የሌለውን የፈጠራ ታሪክ በመለጣጠፍ የኤርትራን መገንጠልና ማስገንጠል ተባባሪ በመሆን የሻዓቢያን ስትራተጂ ለማስፈጸም ህወሓት ምን ያህል ርቀት ሊሄድ እንደሚችልና እንደሄደም በጋሀድ አሳይቶናል። አሳዳጆችንና የአገራችንና የወገናችን ጠላት የሆነውን ሻዓቢያን እዚህ ደረጃ እንዳደረሱትም ግልጽ አድርገው በራሳቸው አንደበት ነግረውናል። የዛሬ አያርገውና “አንጪ መጽኣ ኣላ ሱባጋዲስ ሊእኹዋ ግብሪ ሃብዋ” ተብሎ ሲዘፈን የነበረው ዓጋመ ውስጥ ሳይሆን የዛሬዋ ኤርትራ ውስጥ እንደነበረ ዶ/ር ገላዎዴዎስ አርአያ በአንድ መጣጥፋቸው ውስጥ አስነብበውን ነበር። ይህም የአቶ ስብሓት ነጋን የፈጠራ ታሪክ ጋር ይቃረናል። ዛሬ ያ ሁሉ ቀርቶ ሻዓቢያ እኛን ለመውረር በቃ። ስለዚህ፤ አዎ ሻዓቢያ ኢሮብን ጨምሮ የኢትዮጵያ ቁጥር አንድ ጠላት ነው። ከ100 በላይ ንፁሓን ወገኖቻችንን አግቶ በመውሰድ ደብዛቸውን ካጠፉ ይኸው አስራ ሶስት ዓመት ሊሞላን የቀሩን የተወሰኑ ወራቶች ናቸው። ሆኖም፤ ሐጎስ ዮሐንስ የሚዋደቁለትና ድጋፍ ሊያሰባስቡለት የሚሯሯጡለት የአቶ መለስ መንግሥት ስለነዚህ በሻዓቢያ ስለታገቱ ዜጎቻችን ሲጨነቅ ቀርቶ ሲጠይቅ አልሰማንም። ስለዚህ አሳዳጅ ጋር በመወገን ጥቕማችንንና

የኢትዮጵያን ጥቅም የሚቃረኑ በማውገዝ ፈንታ፤ ሐጎስ ዮሃንስ ታዳኙና ተበዳዩ አብሮ በመቆም ስለበደሉ አብሮ እንዳይጮህ ማኸል በመግባት ውዥንብርና አለመተማመንን ለመፍጠር ሞክረዋል።

ሌላ እዚህ ላይ ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት ጉዳይ ቢኖር፤ ዜግነታዊ መብታችን እንዲከበርልን መጠየቅ ጠላት ጋር የመወገን ትርጉም ሊሰጠው እንደማይገባ ማስገንዘብ ነው። ዳር ድንበራችን ለሻዓቢያና ለሌሎችም እየተለገሠ እያየንና እየሰማን፤ ሥልጣን የጨበጠውን የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝን ስለሚያጋልጥ ብቻ ዝም በሉ ቢባል ትርጉም የሚሰጥ አይሆንም። የዜጎች ሰብአዊ መብት እየተረገጠና እየተገፈፈ ባለበት አገር እንዳላዩ ሆኖ ለማለፍ መሞከር ከአድርባይነትና ከክህደት ውጭ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ተግባር አይሆንም። በፖለቲካዊ አመለካከት ሲለካ፤ ወዳጅና ጠላት የሚፈረጀው እንደ ግለሰብ ለያንዳንዳችን ሊወረወርልን ወይም ሊነፈገን ከሚችለው ጥቅምና ጉዳት አንጻር ሳይሆን፤ ባጠቃላይ ለአንድ አገር ዜጎች ከሚሰጠው ዘላቂ ጥቅምና ጉዳት አንፃር መሆን ይኖርበታል። በመሆኑም፤ ይህ ፀሓፊ ሐጎስ ዮሐንስ መንግሥታችንን ከተቃወምክ ከአሳዳጃችን ጋር ወግነሃል እንዳይሉት በመፍራት፣ ስለ ሉዓላዊ ግዛቶቻችን መከበርና ስለተጠለፉት ዜጎቻችን የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥትን ከመጠየቅ ወደ ኋላ አይልም። ሌሎች ሰብአዊ ህልና ያላቸው ዜጎችም ወደ ኋላ ይላሉ የሚል እምነት የለውም። ስለዚህ ማወገዝም ሆነ ማሞገስ በምክንያት የተደገፈ እንጂ በጭፍን ድርጅታዊ ፍቅር የታወረ መሆን የለበትም።

ሻዓቢያን ደግፎ እዚህ ያደረሰው ማን ሆነና ነው! ሻዓቢያን በመደገፍ የኢሮብ ህዝብንና የኢትዮጵያ መንግሥትን የሚያጣላው? ከዚህ በፊት በህወሓት/ኢህአዴግ መሪዎች በፅሑፍና ለተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን በቃለ ምልልስ መልክ የተሰጡ ማስረጃዎችን በመመርመር ሲታይ፤ ይህ ፀሐፊ ዋናው የሻዓቢያ ደጋፊና አሽቃባጭ አቶ መለስና የተወሰኑ ደጋፊዎቻቸው ናቸው በማለት ለመደምደም ይገደዳል። ይህ በመረጃና ማስረጃ የተደገፈ እንጂ አሉባልታ አይደለም። ሐጎስ ዮሐንስ ለመሸፋፈን ቢሞክሩም፤ ራሳቸው ከሚሉን በመነሳት የሻዓቢያንና የሕወሓት/ኢህአዴግን አቋም ተጋሪ መሆናቸውን ለማሳየት ከባድ አይደለም።

(በሐጎስ ዮሐንስ ፅሑፍ ፓራግራፍ አራት ውስጥ እንደሚከተለው በማለት የሰፈረውን እንመልከት።)

> *“...... በቡናቤቱ ውስጥ ከመጠጥ መደርደርያው በላይ ባለው ግርግዳ ኤርትራ ተገንጥላ የምትታይበት የኢትዮጵያና የኤርትራ ካርታ ተለጥፎ ነበር። አንድ በቢራ ስካር የደነዘዘ የሚመስል ኢትዮጵያዊ መጣና፤ ”ውድ ወዳጄ! እስቲ ካርታውን ተመልከተው! ይህ የኢትዮጵያ ካርታ ይመስላል? ይህንን ካርታ እንደ ኢትዮጵያ ካርታ ቆጥረን መቀበል ይኖርብናል?” ሲል ጠየቀኝ።” “እኔም” “ ጌታየ! ይህ እርሶና እኔ ሮም ውስጥ እንደምናደርገው በቢራ ስካር የተገኘ ውጤት አይደለም! የሚልዮኖች ሕይወት የጨረሰ፤ የዓመታት መራራ ትግል ውጤት ነው። ስለዚህ፣ ወደ ኢትዮጵያ ተራሮችና ጫካዎች ሂድና ጥንት ወደ ነበረችበት መልሳት አልኩት።”*

እዚህ ላይ በጥቅስ ስለተቀመጠው ሓሳብ ክፍል አራት ውስጥ አጭር ትችት በማቅረብ በሌላ ክፍል እንደምንመለስበት ቃል በመግባት ነበር ያኔ የቆመው።

የሐጎስ ዮሐንስ ፅሑፍ ይዞት የወጣው የፈጠራ ውንጀላ ማስረጃና ጭብጥ በማቅረብ ሞግቶ የማሸነፍ ጉልበት የለውም። እሳቸውም ራሳቸው በጽሑፋቸው ውስጥ ደጋግመው እንዳሰፈሩት ይሆናል ብለው የማያምኑት ፈጠራ ቢሆንም፣ መልእክቱ በኤውሮጳና አሜሪካ ነዋሪ የሆኑ የኢሮብ ተወላጆች የኢሮብ ወጣቶችን ለሻዓቢያ እኵይ ተግባር ማስፈጸሚያ ይመለምላሉ የሚል መሆኑ ግልጽ ነው።

በዚህም፤ ሐጎስ ዮሐንስ በባሕር ማዶ የምንኖር ኢሮቦች አሳዳጃችንን በመደገፍ በኢትዮጵያ መንግሥትና በህዝባችን መካከል አለመግባባትን መፍጠር ፍትሐዊም ሕጋዊም አለመሆኑን ያብራራሉ። አሳዳጃችንን መደገፍ ፍትሐዊም ሕጋዊም አይደለም የሚለውን አባባል ይህ ፀሐፊ የሚጋራው ቢሆንም፣ በኢትዮጵያ መንግሥትና በህዝባችን መካከል አለመግባባትን መፍጠር የሚለው አባባል ግን አሻሚ ሆኖ ያገኘዋል። አንድ መንግሥት ለዜጎችና ለአገር ማድረግ ያለበትን ሲያደርግ መደገፍ እንዳለበት ሁሉ ማድረግ የሌለበትን ሲያደርግ ደግሞ መተቸት አለበት ብቻ ሳይሆን አካሄዱን እንዲያስተካክል ማስገንዘብ ተገቢ እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል። በመሆኑም፤ በጠላት ታግተው ከተወሰዱ ወደ አስራ ሶስት ዓመት ሊሆናቸው ወራት የቀራቸው ዜጎችን ለመታደግ የማይፈልግና ምንም ዓይነት ስሜት የማያሳይ፤ የኢትዮጵያን በደም የተከበሩ ሉዓላዊ ግዛቶች አልጀርስና ሄግ በመውሰድ የተከፈለውን መስዋእትነት መና ያስቀረ መንግሥት ባለበት አገር አካሄዱ ልክ አይደለም ማለት መንግሥትና ህዝብ መካከል አለመግባባትን እንደመፍጠር ተደርጎ መቁጠር የለበትም። እንዲያውም አገር ከትውልድ ወደ ትውልድ ዘልቆ የሚሄድ ዘላለማዊ በመሆኑ ላገርና ትውልድ ሲባል መንግሥት ሓላፊ ነውና እንዲህ ዓይነት ጥፋት ባገርና ህዝብ ላይ ሲፈጽም በሕግ-አምላክ! ሊባል ይገባል፤ እንላለንም።

ከዚህ ጋር አያይዘን በኤውሮጳና አሜሪካ ነዋሪ የኢሮብ ተወላጆች ለሻዓቢያ እኩይ ዓላማ ማስፈጸምያ እንዲያገለግሉ የኢሮብ ሕፃናትን እየመለመሉ ወደ አስመራ ይልካሉ የሚለውን የሐጎስ ዮሐንስ ውንጀላ ቀረብ ብሎ መመርመር አገባብ ይሆናል።

ለመሆኑ ሻዓቢያን ለማገልገል የመጀመርያው ረድፍ ላይ ሊሰለፍ የሚችለው ማን ነው? እውነተኛ መልስ ላይ ለመድረስ ከተፈለገ ነገሩን ከሥሩ ማየት ያስፈልጋል። በመሠረቱ ልእለ-ግባዊና (strategic) ስልታዊ (tactical) ተብለው የሚከፈሉ ሁለት መልክ ያላቸው ግንኙነቶች እንዳሉ የሚታወቅ ነው። አንባቢን ላለማሰልቸት ዝርዝ ውስጥ ሳንገባ ስልታዊ ግንኙነት ለልእለ-ግባዊ ግንኙነት ተገዢ እንደመሆኑ መጠን በልእለ-ግብ ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ያላቸው ኃይሎች በተወሰነ ወቅት በተወሰኑ ልዩነቶች ላይ ላይግባቡ ቢችሉም በልእለ-ግባቸው ውስጥ ባለው አንድነት ዘላቂ ጓደኛሞች ማለት ፈረንጆች እንደሚሉት (strategic allies) እንደያዙ ሊዘልቁ ይችላሉ። ስልታዊ ግንኙነት ላይ የተመሠረተ ዝምድና ግን የሚመሠረተው በጊዜያዊ የጋራ ጥቅሞች ላይ በመሆኑ ያ ያገናኛቸው ጉዳይ እንዳበቃ የሚያበቃ ይሆናል። ህወሓት/ኢህአዴግና ሻዓቢያ ደግሞ ኤርትራን ነፃ የማውጣት ልእለ-ግብ ላይ ያላቸው የአቋም አንድነት ንቅንቅ የማይል እንደሆነ የሚታወቅና እነሱም በግልጽ የነገሩን አቋማቸው ነው። ስለዚህ፤ ከላይ እንደተገለጸው በልእለ-ግብ የሚሰማሙ ኃይሎች መካከል የሚኖረው ስልታዊ ቅራኔ፤ ልእለ-ግብ ለስልት ተገዢ ይሆናል እስካልተባለ ድረስ ሊኖር የሚችል አይደለም። ስለሆነም ነው ከላይ የሚደመጠው የአቶ ስብሐት ነጋ ቃለ-ምልልስ ኤርትራን የነካ ወዮለት የሚለንም መነሻው ከዚህ አቋም ነው ሊሆን የሚችለው። ለኤርትራ ነፃነት ሲባል ኢትዮጵያ መክፈል የነበረባት፤ እየከፈለችው ያለውና ገናም የምትከፍለው እዳ እዚህ በማስፈር የሚያልቅ ስላልሆነ ባይነካ ይሻላል። የሆነ ሆኖ እዚህ ማስጨበጥ የተፈለገው ነጥብ ሐጎስ ዮሐንስ ከአለቆቻቸው ከነአቶ መለስ ዜናዊና አቶ ስብሐት ነጋ ባልተናነሰ የሻዓቢያን ልእለ-ግብ ደጋፊ ሆነው መውጣታቸው በምንም መልኩ ጥርጣሬ ውስጥ ሊገባ የምችል አለመሆኑን ነው። በመሆኑም፤ የማታ የማታ በልእለ-ግብም ሆነ በስልት ደረጃ ሊደጋገፉና የጥቅም ተጋሪ ሊሆኑ የሚችሉት ህወሓት/ኢህአዴግና ሻዓቢያ እንደሚሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም። ባጭር አባባል በልእለ-ግብ ላይ የተመሰረተ ግንኙነት በስልት ሊፈርስ አይችልምና፤ ሐጎስ ዮሐንስ የሻዓቢያን ልእለ-ግብ እየደገፉ አለቆቻቸው በመካከላቸው በተነሳው ጊዜያዊ ስልታዊ ቅራኔ ምክንያት ሲሳደቡ

ስለሰሙ ራሳቸውን የሻዓቢያ ጠላት በማስመሰል ሌሎችን የሻዓብያ ወዳጆች አድርጎ ለማቅረብ መሞከር ትርፉ ትእዝብት ብቻ ነው። ቀጥሎ ያለውን እንመልከት!

ሐጎስ ዮሐንስ *“ ጌታየ! ይህ እርሶና እኔ ሮም ውስጥ እንደምናደርገው በቢራ ስካር የተገኘ ውጤት አይደለም! የሚልዮኖች ሕይወት የጨረሰ፣ የዓመታት መራራ ትግል ውጤት ነው።”* በማለት አንድ ኢትዮጵያዊ ወንድማቸውን ሮም ውስጥ የአንዲት ኤርትራዊት እመቤት ንብረት በሆነው ቡናቤት ውስጥ መሞገታቸው “ሲያበስሩን”፤ የሻዓቢያ አቋምና ስትራተጂያዊ ግብን እደግፋለሁ እያሉን መሆኑ ልብ ልባል የሚገባው ጉዳይ ነው። አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያመለክቱትና ሻዓቢያ ራሱም እንዳመነው በ30 ዓመታት “የነፃነት” ትግል በጠቅላላ የ60.000 (ስልሳ ሺ) ታጋዮች ሕይወት እንደተከፈለ በይፋ ተናግሯል። ሐጎስ ዮሐንስ በጽሑፋቸው ውስጥ “…የሚልዮኖች ሕይወት የጨረሰ…” ይሉታል። ሰዎች! “ከጳጳሱ በላይ ካቶሊክ..” የሚባለው እንዲህ ሲሆን ይሆን? ለማነኛውም አንባቢ የሚለው ይበልበት። የሆነ ሆኖ ሐጎስ ዮሐንስ የአቶ መለስና አቶ ስብሐት ነጋን አቋም አራማጅና አቀንቃኝ መሆናቸው የሚያጠራጥር አይደለም። ይህም አቋማቸው በቀጥታ የሻዓቢያ ልእለ-ግብ ደጋፊ (strategic ally) ያደርጋቸዋል። በግራም ተባለ ቀኝ ግን ለሻዓቢያ ተልእኮ ማሳኪያ እንዲያገለግሉ የኢሮብ ሕፃናትን የሚመለምሉ የኢሮብ ተወላጆች አሉ የሚለው ሙግት ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች በአመክንዮም ሆነ በማስረጃ ሊደገፍ ያልቻለ ቅጥፈት ከመሆን ለማለፍ አልቻለም።

ከዚህ በተረፈ፤ አቶ ስብሐት ነጋ በ2007 ዓ.ም.ፈ ለወይን ጋዜጣ በሰጡት ቃለ-ምልልስ ኤርትራን የነካ ወዮለት ከማለት አለፈው አንዳንድ የኤርትራ ድርጅቶች የኤርትራ ነፃነት ላይ መለሳለስ ባሳዩበት ወቅት ሳይቀር ህወሓት ለኤርትራ ነፃነት ከነሱ በላይ ቆሞ እንደሞገተና እንደተዋደቀ የነገሩን የሻዓቢያን/ኤርትራን የመገንጠል ልእለ-ግብ ያለ ምንም ቅድመ-ሁኔታ መደገፋቸውን በግልጽ ያመለክታል። ስለሆነም፣ በልእለ-ግብ (በስትራተጂ) ደረጃ ሻዓቢያ ጋር በመወዳጀት የአገራችንን ዘላቂ ጥቅም አሳልፈው የሰጡት የህወሓት/ኢህአዴግ መሪዎች ናቸው። ስለሆነም የሁለቱ ቅራኔ አንዱ በሌላው ሥልጣን ላይ ሊያስከትለው ከሚችለው አደጋ አንጻር እንጂ ከልእለ-ግብ አንጻር ስላልሆነ፤ አንዱ የሌላውን ሥልጣን አደጋ ላይ የማይጥል መሆኑ ከተረጋገጠ ያለ የሚመስለው ቅራኔ በአንድ ጊዜ ተኖ ሊጠፉ የሚችል እንደሆነ ልብ ሊባል ይገባል። ሐጎስ ዮሐንስ ከሻዓቢያ ጋር ያላቸው ቅራኔም (በውነት ቅራኔ ካላቸው) አለቆቻቸው ከቋጠሩት ስልታዊ ቅራኔ የተለየ ሊሆን አይችልም። “ተከተል አለቃህን…..” ይባላልና ሐጎስ ዮሐንስም አለቆቻቸው ከሻዓቢያ ጋር እርቅ ሲፈጥሩ የሚታረቅ ቅራኔ እንደሆነ ያላቸው ልብ ሊባል ይገባል።

ከዚህም ሌላ ዛሬ ሐጎስ ዮሐንስ “አሳዳጆችን” የሚሉት ሻዓቢያን እዚህ ያደረሰው ህወሓት/ኢህአዴግ መሆኑ መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ ነው። በመጀመርያ ደረጃ ምንም ታሪካዊ ማስረጃ ሳይቀርብ ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነበረች የሚለውን ተራ በእውቀት ላይ ሳይሆን በድፍረት ላይ የተመሠረተ አቋም ወስዷል። በሁለተኛ ደረጃ፤ ከዚህ ተራ የድፍረት አቋም በመነሳት ምንም ታሪካዊ ጭብጥ ሳያቀርቡ፣ ቅድመ-ሁኔታዎችም ሳይሟሉ ጉዳዩን ለማቀላጠፍ እንዲተባበራቸው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን እየለመኑ የኤርትራን መገንጠል ተግባራዊ አድርጓል። ያኔ የተነገረን፤ ከእንግዲህ ወድያ ጦርነት ታሪክ ሆኗል፣ በአከባቢያችንም ዘላቂ ሰላም አንግሰናል! እየተባለ የተነገረን ሁሉ እንዳልሆነ ሆኖ ወረራ ተከፍቶብን የከፈልነው ዋጋ ለመገመት የሚያዳግት ነው። ሐጎስ ዮሐንስ ግን ይህንን ተግባር ለመኮነን የሞራል ብቃቱ ስለሌላቸው “አህያውን ፈርቶ ዳውላውን” እንደሚባለው መወቀስ ያለበትን በማወደስ አመልካች ጣታቸውን ወደ አልሆነ አቅጣጫ ለመቀሰር መርጧል። ቀኑ ሲወጣና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሻዓቢያ ኤምባሲ ጓዳ ውስጥ ሲሽሎኮለኩ

የነበሩ እነማን እንደሆኑ ህዝብ እንዲያውቀው ይፋ ይደረጋልና መጠበቅ ነው። ለማነኛውም፤ በሻዓቢያ ደጋፊነት በመጀመርያ ደረጃ ሊጠረጠር የሚገባው "የሚልዮኖች ሕይወት ያስፈጀ፤ የዓመታት መራራ ትግል ውጤት" የሚለው የሻዓቢያን ዓላማና ግብ የሚደግፍ ወገን ነውና ሐጎስ ዮሐንስና መሰል ወዶ-ገብ ካድሬዎች ከሻዓቢያ ጋር የሚያወዳጃቸው ልእለ-ግብን (ስትራቴጂ) ቢመረምሩት ይበጃቸዋል። ነገሮች ተሸፋፍነው የሚቆዩት ለተወሰነ ጊዜ ብቻ መሆኑን ልብ ማለት ብልህነት ነው።

(በፓራግራፍ 8 ከ10ኛ መስመር ጀምሮ እንዲህ የሚል ሰፍሯል)

> *"እያልኩ ያለሁት እንዲህ ነው፤ እኔ ፈጽሞ ለማመን የማይቻለኝ ነገር ቢኖር፤ በርካሽ ፍላጎት ተነሳስቶ የኢሮብ ሕፃናትን ጋብዞ በማደራጀት ከወላጆቻቸው ገዳይ፤ የሰላማቸው፣ አገራቸውንና ንብረታቸውን አውዳሚና አደፍራሽ ጎን በማሰለፍ የኢሮብ ህዝብን ለማስፈጀት የሚነሳሱ የኢሮብ ተወላጆች አሉ የሚለውን ነው።"*

ሐጎስ ዮሐንስ እዚህም የሚደግሙት በጽሑፋቸው ውስጥ ከመጀመርያ እስከ መጨረሻ ድረስ የሚታየውን በራስ ያለመተማመን አባዜ ነው። እውነትን ከጨበጡና ለማስፈራራት "እንበለውና" እንደሚሞክሩት ጭብጡ በእጃቸው ካለ! ፈርጠም ብለው፤ ነገሮችን ግልጽልጽ በማድረግ፤ አለኝ የሚሉት መረጃን ጀባ ብለውን መከራከርና እውነትን በማስጨበጥ ሚስጥሩን እንድናውቅ ማድረግ እንጂ፤ ይህንን ራሳቸው ያላመኑበትን ሐሳብ ይዞ ገበያ በመውጣት ራሳቸውን ለትእዝብትና ቅሌት መዳረግ አልነበረባቸውም። ሐጎስ ዮሐንስ! እውነቱን ለመናገር ከሆነ፣ ፅሑፉዎ ለሆነ ግብ ሲሉ የፈጠሩት ወሬ ከመሆን የዘለለ ፋይዳ የለውም። በመሆኑም፤ ይህ ቅሌት በሕይወትዎ ውስጥ የጎሊና (ጤናማ ጎልና ካሉዎት ማለት ነው) ውጋት ሆኖብዎት እንደሚኖር አያጠራጥርም።

(ፓራግራፍ 8 ከ16ኛው መስመር ጀምሮ እንዲህ የሚል ሰፍሯል)

> *"…. ይህንን ተከትሎም፤ሁሉም የኢሮብ ተወላጆች ሻዓቢያ ይህንን ሁሉ እንዳፈራረሰ ያምናሉ። በመሆኑም ለኔ ሻዓቢያን ለመጥቀም የኢሮብ ቡድኖችን አቀናጅቶና አደራጅቶ የኢሮብ ህዝብንና ኢትዮጵያዊያንን ለመፍጀት የሚነሳሳ አንድ የኢሮብ ሰው የለም ብሎ ማመን ይበልጥ አመክንዮዊ ነው።"*

ነፍሱን ይማረውና "አለቀ ደቀቀ" ነው ያለው ጋዜጠኛ ዓለም መዝገበ! አመክንዮአዊ የሚሆነው ይህንን ተግባር የሚፈጽም የኢሮብ ተወላጅ የለም የሚለው ከሆነ፤ ይህንን ሁሉ ዝባዝንኬ መጻፍ ለምን አስፈለገ? ነገሩ በዚህ ተዘጋኮ ጃል!

(ፓራግራፍ 9 ከ5ኛው መስመር ጀምሮ እንዲህ የሚል ሰፍሮ ይገኛል)

> *"….. ይሁን እንጂ እነዚህ አሉባልታዎች እውነት ሆነው ከተገኙና ሕፃናቶቻችንን በጦርነትና እሳት ለመማገድ ለግል ጥቅማቸውም ሆነ የኢትዮጵያን መንግስት፤ ሕወሓት፤ ወይም በኢትዮጵያ መንግስት ውስጥ የሓላፊነት ቦታን የያዘ ግለሰብ ለመበቀል ከዛሬው ሻዓቢያ ጎን በማሰለፍ ተግባር ውስጥ የሚሳተፉ አንድ ሰውም ይሁን ቡድን ቢገኝ፤ ሁሉም የኢሮብ ተወላጅ አንድ ላይ ቆሞ በመመከት ይህን ዓይነት አሳፋሪ ባሕሪና ተግባርን ማስቆም መቻል አለበት።"*

እውነት ነው! ይህንን ዓይነት ተግባር ማስቆም መቻል አለብን። ማስቆም ብቻም ሳይሆን ይህንን ዓይነት የወንጀል ተግባር ውስጥ እጃቸውን የከተቱ ቡድኖችም ሆኑ ግለሰቦች ካሉ ለሕግ ቀርበው ተገቢ ፍርድ ማግኘት ይኖርባቸዋል። ስለሆነም፤ የሐጎስ ዮሐንስ በጽሑፍ የሰፈረ! የማይሻር ምርጥ ያሉትን መረጃ ሊያቀርቡልን ይገባል። አንባቢም ይህንን እንዲያደርጉ ሊያበረታታቸው ይገባል።

(ፓራግራፍ 9 ከ10ኛ መስመር ጀምሮ እንደሚከተለው የሚል ሰፍሮ ይገኛል)

> *"በውጭ አገር ለምንኖር የኢሮብ ተወላጆች ግልጽ መሆን ያለበት ጉዳይ ጠላታችንን ለመደገፍ ስንል በኢሮብ ህዝብና በኢትዮጵያ መንግስት መካከል ቅራኔ እንዲፈጠር ካደረግን የራሳችን በሆነው የኢሮብ ህዝብ ላይ ኢ-ፍትሐዊና ሕገ-ወጥ ተግባር እየፈጸምን መሆናችን ነው።"*

እዚህ ላይ ሐጎስ ዮሐንስ የሚወነጅሉት በውጭ አገር ነዋሪ የሆነውን የኢሮብ ተወላጅ በሙሉ ነው። የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊና ደግ መንግሥት ከሆነና ህብረተ-ሰቡ ያንን ደግነት አምኖ ከተቀበለ፤ መንግሥቴ ላገርና ለህዝብ የሚበጅ ሥራ እየሠራ ነው ብሎ ከተቀበለ፤ ህዝብና መንግሥት መካከል ቅራኔ የሚፈጠርበት ምክንያት ምን ሊሆን ይችላል? የህዝብ ጥያቄ ሁሌም ፍትሕ እንዲኖር፤ ሰብአዊ መብቱ እንዲከበር፤ መሠረተ-ልማት እንዲስፋፋ፤ በአከባቢው ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍን፤ ፍትሕ ለሁሉም ያለአድልዎ እንዲዳረስ.... ወዘተ ነው። እነዚህ ከተሟሉለት ህዝብ ከመንግሥት ጋር ቅራኔ ውስጥ የሚገባበት ምክንያት አይኖረውም። ቅራኔን የሚጋብዙ የመብት ረገጣዎች እስካሉ ግን ሐጎስ ዮሐንስም ሆኑ ሌላ ወዶ-ገብ ካድሬ ቢነሳ ቅራኔውን የማስወገድ አቅም አይኖረውም። መንግሥት ዳር ድንበርን አስወርሮ ሉዓላዊ ግዛታችንን ወዶና ፈቅዶ በዓላማ ለሚገባባው ወገን ሲያድል ህዝብ መርቆ መቀበል አለበት የሚል አስተሳሰብ ካለ የተሳሳተ ነው። መርቆ መቀበል ሳይሆን ቆርጦ መፋለም አለበት። ሕዝባችን የተወረረ ጊዜ የመጀመርያው ደራሽ መንግሥታችን፤ ሕወሓትና ህዝብን ለማገልገል የተመደቡ ወገኖች ነበሩ የሚለውን ቀልድ ሁሉም ስለሚያውቀው ትርጉም የሚሰጥ አይደለም። መንግሥትና ሕወሓት ስለደረሱ ነው አከባቢያችን ለሁለት ዓመት በሻዓቢያ አውዳሚ ሠራዊት ቁጥጥር ሥር የቆየው? ዓይጋ ላይ የጦርነቱ የመጀመርያ ወላፈን የበላቸው ጀግኖቻችን ሕይወታቸውን የከፈሉት መንግሥት ስለደረሰላቸው ነበር?

በመጨረሻ ላይ ሐጎስ ዮሐንስ በፓራግራፍ 11 ወደ መጨረሻ አከባቢ እንደሚከተለው በማለት ያሰፈሩት ነጥብ አለ፤ ይኸውም፡

> *"....... ደግሞም በምንም ዓይነት መንገድ ሊጠፋ የማይችል እሳትን መለኰስ ነው።"*

ሐጎስ ዮሐንስ! እውነት ይህንን ያቀረቡትን ወንጀል የፈጸመ ሰው ካለ! (ቅጥፈቱ ግልጽ ስለሆነ "ካለ" የሚለውን ጠበቅ አርጎ መድገም ያስፈልጋል) ካለ! የለኰሰውን እሳት የማጥፋት ግዴታ እንዳለበትና ላደረሰው ጥፋትም በሕግ ተጠያቂ መሆን እንዳለበት ይህ ፀሐፊም ያምናል። ሆኖም እርስዎ ራስዎ በፈጠራ ወሬ የለኰሱት እሳትም ካለ (እንዳለ ባያጠራጥርም) ካለ ብለን መዓርግ ባለው መልክ እናስፍረውና፤ የለኰሱትን እሳት የማጥፋት ግዴታ እንደሚጣልብዎት ሊገነዘቡት ይገባል። ለሁሉም ጊዜ ይስጠን እንጂ እውነቱ መጋለጡ አይቀርም። ያኔ የሚያፍር ያፍራል!!!

ይቀጥላል.................!!!          የካቲት ቀን 2012 ዓ.ም.ፈ

ለአስተያየት balibizema@yahoo.com ይጠቀሙ!